# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TWENTY-FIVE: አናዳጅ ክስተቶች

**Author: Chrispin Mwakideu**

**Editor: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

## SCENE 1: አቶ ሙላቱ AND FAMILY ARRIVE HOME

- አቶ ሙላቱ (M, 45)
- ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)
- ብሩክ (M, 8)
- ቅዱስ (M, 8)
- ፖሊስ ሙሉጌታ (M, )

## SCENE 2: ምህረት 'S PREGNANCY TEST IS POSITIVE

- ዶ/ር ዘሪሁን (M, 45)
- ምህረት (F, 15)
- ትዕግስት (F, 15)

## SCENE 3: ንጉሴ AND ዳንኤል TAUNT EACH OTHER AT SCHOOL

- ንጉሴ (M, 16)

- ዳንኤል **(M, 16)**

- ምህረት **(F, 15)**

## SCENE 4: ወ/ሮ ሉሊት, TWINS AND አቶ ካሳሁን MEET AT ምህረት 'S SCHOOL

- ቅዱስ **(M, 8)**

- ወ/ሮ ሉሊት **(F, 40)**

- ብሩክ **(M, 8)**

- አቶ ካሳሁን **(M, 50)**

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን ዉድ የበማድመጥ መማር ተከታታዮች። ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ ከዶይቼ ቬለ ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉ ድራማ ነዉ። እስቲ ያለፈውን መለስ ብለን እናስታውስ።

ምህረትን ፈታኝ ጊዜ ገጥሚታል። የወር አበባዋ አልመጣም። ይህንንም መጥፎ ፍርሀቷን ለጓደኛዋ ትዕግስት ስታማክርም ትዕግስት ዶክተር ጠርታ ነበር።

2. ዶ/ር ዘሪሁን **(EP 24, 94):** "እርግጠኛ እንድንሆን የእርግዝና ማረጋገጫ ምርመራ እናድርግ። (…)ከዛ በኋላ የተሸከምሽው ነገር እንዳለ እናውቃለን። "

3. *ምህረት : "የተሸከምሽው ነገር ?ምን ህፃን ልጅ ማለታቸው ነው? መቼም እንደዛ እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ።!"*

በሌላ በኩል አቶ ሙላቱ ከባለቤታቸው ጋ ገጠር ውስጥ ተገናኝተዋ። ባለቤታቸው ወ/ሮ ሉሊት በትዳራቸው ደስተኛ ባልሆኑበት ወቅት ወደ ወላጆቻቸው ዘንድ ገጠር ሄደው ነበር። አቶ ሙላቱ የቀድሞ ቀጣሪያቸው የአቶ ጃለታን ንብረት በመዝረፍ ተጠርጥረዋል። ባለቤታቸውንም እንዲረዷቸው አሳምነዋል።— ኋላም ከአውቶቢስ ወርደው ወደ ቤታቸው በመሄድ ላይ ሳሉ አስደሳች ሁኔታ አጋጥሟቸዋል።!

4. ቅዱስ (EP 24, LINE 60): "ብሩክ! ብሩክ ! ተመልከት… (shouting) እማዬ እማዬ!"

5. ወ/ሮ ሉሊት: "ሙላቱ ይሰማሀል??" + "እማዬ እና አባዬን አዛጋ ተመልከት።!"

6. ወ/ሮ ሉሊት: "ውይ ውይ ሙላቱ - እኔ አላምንም። ከመንገዱ ማዶ ተመልከት። ቅዱስ እና ብሩክ ፤ ልጆቻችን ናቸው የሚጠሩኝ!"

7. አቶ ሙላቱ : "ምን? የቱጋ? ...እውነትም እነሱ ናቸው! እኛውና!"

ወ/ሮ ሉሊት እና አቶ ሙላቱ ከመንታ ልጆቻቸው ቅዱስ እና ብሩክ ጋ ተቀላቅለዋል። ታስታውሱ እንደው ልጆቹ ከሚያሳድጓቸው አክስታቸው ከላቦሪያ ጠፍተው ነው የመጡት። ብቻ የቤተሰቡ ቅልቅል ዘለቄታ ይኖረው ይሆን?

ይህ 25ኛው እና አናዳጅ ክስተቶች የተሰኘው ክፍል ነው። ከአቶ ሙላቱ ፣ ወ/ሮ ሉሊት፣ ከ ልጆቻቸው ቅዱስ እና ብሩክ ጋር ነው የምንጀምረው። መሽቷል። ቤተሰቡም ወደ አዲሱ ቤት እየገባ ነው።

## SCENE 1: አቶ ሙላቱ AND FAMILY ARRIVE HOME

**8. ATMO SUBURB IN THE EVENING**

**9. SFX: FOOTSTEPS OF PEOPLE WALKING TOWARDS HOUSE**

10. አቶ ሙላቱ : በሉ ልጆች እቤታችን ደርሰናል። ከታንዲካ ለቀን እዚህ የምታዩት ቤት ገብተናል። ምን ትላላቹህ?

11. ቅዱስ: (excited) አባዬ! ይህ አዲሱ ቤታችን ነው?

12. አቶ ሙላቱ : አዎ ቅዱስ ። እዚህ ነው ከአሁን በኋላ የምንኖረው።

13. ብሩክ : በስመዓም! ከበፊቱ ቤታችን በጣም ይበልጣል።

14. SFX: DOOR BEING UNLOCKED AND OPENED

15. ወ/ሮ ሉሊት: (shocked by scene of devastation) የፈጣሪ ያለ። ምን ጉድ ነው ሙላቱ? እግሬ ወጣ ቢል ተመልከት ቤቱ እንደዚህ መላ ቅጡ ጠፍቶ ጠበቀኝ። ምህረት የታለች ? በአሁን ሰዓት እቤት መሆን አልነበረባትም?

16. አቶ ሙላቱ: (also surprised) ሉሊት በእውነት ቤቱ ውስጥ ምን እንደተከሰተ የማውቀው ነገር የለም። ልጆች ከእናታችሁ ጋ ቆዩ። እቤቱ ውስጥ ሰው እንዳለ ላረጋግጥ። (calls out) ምህረት ! ቤት ውስጥ አለሽ?

17. SFX: FOOTSTEPS WALKING ON GLASS AND SCATTERED BELONGINGS

18. SFX: DOOR CLOSED

19. ብሩክ : እማዬ! የድሮው ቤታችን ታንዲካ እንሂድ። ይህኛው ቤት ትልቅ እና አስፈሪ ነው።

20. ወ/ሮ ሉሊት: አይዟችሁ ልጆች አሁን ከኛ ጋ ናቸሁ። ዋናው ነገር እሱ ነው። ከእንግዲህ ማንም እንዲወስዳችሁ አልፈቅድም።

21. SFX: DOOR SUDDENLY CRASHES OPEN

22. ወ/ሮ ሉሊት: (screams in fear) ውይ ሙላቱ! ድረስ!!

23. ቅዱስ / ብሩክ : ,ወይኔ!

24. ፓሊስ ሙሉጌታ : (commanding voice) ባላችሁበት ቁሙ። ማንም እንዳይንቀሳቀስ። በመጨረሻ ቀማኛውን ይዘነዋል። ይህንን ቤት በአይነ ቁራኛ ስንጠብቅ ነበር። ታድያ ዛሬ አይጡ ወጥመዱ ውስጥ ገብቷል።አቶ ሙላቱ እጅህን ወደላይ አድርገህ ካለህበት ውጣ!

**KW BEGIN**

**25.** ወ/ሮ ሉሊት: **(pleading)** እባክህ ባለቤቴን ምንም እንዳታደርገው። በፈጠረህ ይዤሀለሁ። ምንም የፈፀመው ወንጀል የለም።

**26.** ብሩክ : **(supporting)** አባቴ የሰዎችን ደህንነት የሚጠብቅ ነው። ዘበኛ ነው። መጥፎ ሰው አይደለም።

**27.** ፖሊስ ሙሉጌታ : ና ወደዚህ።

**28.** አቶ ሙላቱ : **(breathing audibly)**

**KW END**

**29. SFX: FOOTSTEPS WALKING SLOWLY ON SCATTERED MATERIALS**

**30.** ፖሊስ ሙሉጌታ: እጅህን እንዳታወርድ። በጣም አዝናለሁ። ይህንን ቤተሰብህ ፊት ማድረግ ,ለብኝ፤ሌላ አማራጭ አልተውክልንም። አቶ ሙላቱ እጅህን ዘርጋ።

**31. SFX: HANDCUFFS BEING PUT ON AND SNAPPED SHUT**

**32.** ወ/ሮ ሉሊት: **(begins to cry)** ባለቤቴ ምን አጥፍቶ ነው።

**33.** ቅዱስ: **(crying)** እባክዎ አባታችንን አይውሰዱት…

**34.** ብሩክ : **(also weeping)** ከረዥም ጊዜ በኋላ ገና መገናኘታችን ነው። እባክዎን

**35.** አቶ ሙላቱ : አይዞዋችሁ ልጆች። አባታችሁ ተመልሶ ይመጣል። እናንተ እናታችሁ ጋ ቆዩ። ሉሊት ምህረትን ፈልጊያት። ወይ ትምህርት ቤት ወይ ትዕግስት ጋ ነው የምትሆነው። ጓደኛዋ ናት። ግን የት እንደምትኖር አላውቅም። ልጆች አይዟችሁ አትጨነቁ ቶሎ እመለሳለሁ።

**36.** ፖሊስ ሙሉጌታ : አቶ ሙላቱ! መሰናበቱ ይበቃል። ተንቀሳቀስ። የምትፈለግ ሰው ነህ።እንዲሁ በቶሎ መመለስህን እንጃ።

**37. አቶ ሙላቱ :** **(sighs)**

**38. SFX: MUSIC INTERLUDE**

**SCENE 2: ምህረት ’S PREGNANCY TEST IS POSITIVE**

**39. ATMO: ትዕግስት 'S ROOM IN THE EVENING, LIGHT TRAFFIC OUTSIDE**

**40. ምህረት :** ትዕግስት ውጤቱን ለማወቅ ለምንድን ነው ይህን ያህል ጊዜ የሚፈጀው? ጭንቀቱ ሊገለኝ ነው። ተመልከች እንዴት መላ አካላቴ በላብ እንደተዘፈቀ።

**41. ትዕግስት :** ተረጋጊ ምህረት ። ዶ/ር ዘሪሁን ከደቂቃ በኋላ ይመለሳል።

**42. ምህረት :** ከአንድ ቀቂቃ በፊትም ያልሸኝ ይህኑኑ ነበር። ግን ረዥም ደቂቃ ወስዶባቸዋል ሲመስለኝ --

**43. SFX: KNOCK ON DOOR, DOOR OPENING, FOOTSTEPS COMING IN**

**44. ዶ/ር ዘሪሁን :** ምህረት ። እስቲ ተቀመጭ። ምርመራውን አጠናቅቄያለሁ። ውጤቱ የሚያሳየው ...ነፍሰ ጡር መሆንሽን ነው።

**45. ምህረት :** **(resigned)** ወይኔ ጉዴ። መሞት ነው የሚሻለኝ።

**46. ትዕግስት :** ምህረት እንደሱ አትበይ። እኔ... **(hesitant)** እኔም... ከዚህ ቀደም... ገባሽ?! አርግዤ አውቃለሁ። ፍርዱ ሞት አይደለም። ሊደረጉ የሚችሉ... አማራጮች አሉ።

**47. ምህረት:** **(shocked)** ምን አልሽ?

**KW BEGIN**

**48. ትዕግስት :** ዶክተር እባክዎ ያስረዷት።...

**49. ዶ/ር ዘሪሁን :** ትዕግስት ልክ ነች ምህረት ። ግን ትዕግስት ፅንስን ማስወረድ እንደ ቀላል ነገር ያየሽው ይመስለኛል።

**50. ትዕግስት :** **(shrugging his words off)** አዎን ልክ ነዎት ዶክተር። ምህረት

ባለፈው አመት ብቻ ሁለት ጊዜ አስወርጃለሁ።

**51.** ምህረት: **(surprised)** ምን?

**KW END**

**52.** ዶ/ር ዘሪሁን : ፅንሱን ያስወረደችው ገና እንደፀነሰች ነበር። ወላጆቿ እንኳን ስለዚህ የሚያውቁት ነገር የለም። ለዛ ነው እኔ...ፅንስ ለማስወረድ የሚፈልጉ ወጣት ልጆችን የምረዳቸው። ያው ግልፅ ነው። በክፍያ ነው።

**53.** ምህረት: **(still shocked)** ትዕግስት! ከአንዴም ሁለቴ ፅንስ አስወርጄያለሁ ነው ያልሺው? እንዴት አድርገሽ?

**54.** ትዕግስት : አየሽ ገና ወጣት ነበርኩ እና --

**55.** ዶ/ር ዘሪሁን : ትዕግስት አሁንም ወጣት ነሽ። እውነቱን ንገረን ካላችሁ ሁለታችሁም ገና ልጆች ናችሁ ከወንዶች ጋ እንደዚህ አይነት ድርጊት ለመፈፀም። በሌላ በኩል እናት ለመሆንም ገና ትንሽ ናችሁ። እንግዲህ የራሳችሁ ምርጫ ነው። ስራዬን አጠናቅቄያለሁ። ትዕግስት ያው እንደተለመደው ሂሳቤን እፈልጋለሁ።

**56.** ምህረት: **(realizing)** እኔ አላምንም እርጉዝ ነኝ ማለት ነው? ። በውስጤ የዳንኤልን ልጅ ተሸክሜያለሁ ...

**57.** ዶ/ር ዘሪሁን : በሉ ልጆች ልሂድ። መሽቷል። ከፈለጋችሁኝ የት እንደምታገኙኝ ታውቃላችሁ።

**58.** ትዕግስት : ለርዳታዎ አመሰግናለሁ ዶክተር ዘሪሁን... ይኼው ገንዘቡ።

**59. SFX: BANK NOTES HANDED OVER, COUNTED OUT**

**60.** ዶ/ር ዘሪሁን : አመሰግናለሁ። ትዕግስት።በሌላ ጊዜ እስከምንገናኝ ደህና ሁኑ።

**61. SFX: FOOTSTEPS, DOOR OPENED AND CLOSED**

**62.** ምህረት : **(deep breath)** እኔ አሁንም ማመን አልቻልኩም።

**63.** ትዕግስት : ተረጋጊ ምህረት። አንድ ቀን አረፊበት እና ነገሮች ነገ ሌላ ገፅታ ይኖራቸዋል።

**64.** ምህረት : **(close to tears)** አመሰግናለሁ ትዕግስት ።

**65. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 3: ንጉሴ AND ዳንኤል TAUNT EACH OTHER AT SCHOOL</u>**

**66. SFX: SCHOOL YARD IN THE MORNING**

**67. ንጉሴ:** **(shouts)** እንዴት አደርክ ዳንኤል! ስማ! ቆይ እንጂ...አንድ ነገር ልነግርህ እኮ ነው። የቦንጎ አካዴሚን ለቀህ ልትሄድ በመሆኑ አዝናለሁ። ልትለየን በመሆኑ ሁላችንም ቅር ተሰኝተናል።**(starts to laugh)**

**68. ዳንኤል:** **(sarcastic)** ሀ ሀ ሀ...እንዴት ያስቃል! እንዴት እንደሚቀለድ እንኳን አታውቅበትም። አንተ አሳዛኝ ትንሽ የማሚ ልጅ!

**KW BEGIN**

**69. ንጉሴ :** አሳዛኝ? ከምርህ ነው? ከክፍል በለጥኩህ። በእኔ እንዳታሾፍ ነገርኩህ። ሀይለኛውን ኃያሉን ንጉሴ ጃለታን ከተዳፈርክ የምታገኘው ይሄን ነው። **(chest thumping)**

**70. ዳንኤል :** ደረትህን እንደሱ ስትደልቅ። የሆነ ደደብ ዝንጀሮ ነው የምትመስለው። ከክፍል ሰቃይ ልትሆን ትችላለህ። ግን የሆንክ ምስኪን ቢጤ ነህ ንጉሴ። በተለይ ሴት መጥበስን በተመለከተማ ይህ ፀባይህ ዱልዱም ቢላዋ ነው። ተመልከት እኔ ከክፍላችን ጎበዝ እና ውቧን ምህረትን ነው የጠበስኩት።እንዴት ነው ይሄ ደረት አያስመታም?**(chest-beating too)**

**KW END**

**71. ንጉሴ :** እስቲ አስበው አንተ አገር ለቀህ ስትሄድ ምህረት ዞር ብሎ የሚያያት ሰው የለም። ያኔ ማን ጋ እያለቀሰች የምትሄድ መሰለህ?

**72. ዳንኤል :** ትዕግስት ጋ ነዋ። አንተ ጋ በፍፁም አትመጣም ንጉሴ ! ደሞ አንተ ጋ ብትመጣስ ምን ይጠበስልህ? እኔ እንደው ማሩን ከቀፎው ቀምሼዋለሁ። የመጀመሪያዋ እኔ ነበርኩ።

73. ንጉሴ : (angry) ሁሌም መዋሸት ስለምትወድ በጭራሽ አላምንህም። ምህረት ይህን እንደማታደርግ አውቃለሁ።

74. ዳንኤል : አመንከኝ አላመንከኝ የኔ ጉዳይ መሰለህ! ደግሞ እንድታውቀው ያህል ሌላ ልጃገረድ ሀገሬ እየጠበቀችኝ ነው። እና መገመት እንደምትችለው በጣም ተወዳጅ ነኝ።

75. ንጉሴ : ስልጣን ቢኖረኝ ኖሮ ቀጥሎ በሚሄደው አውሶቢስ፣ጀልባ ፣ግመል ወይንም ሀገሬ በመጣህበት ማንኛውም መጓጓዣ ነበር አሳፍሬ ወደ ሀገርህ የምልክህ ።

76. ዳንኤል : ሃ ሃ ሃ ሃ… ችግርህ እኮ ይኼ ነው ንጉሴ። በኔ ላይ ያለህ ብቸኛ ስልጣን የክፍል አለቃ መሆንህ ብቻ ነው። ከትምህርት ቤት ግቢ ውጪ ምንም ማለት ነህ።

77. ንጉሴ: (about to start a fight) አንተ ጅል! ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ አንድ ትምህርት አስተምርሃለሁ።…

78. ምህረት: (from afar) ዳንኤል! አንዴ ጠብቀኝ!

79. SFX: FOOTSTEPS RUNNING

80. ንጉሴ : እድለኛ ነህ! አዳነችህ! በኋላ አገኝሀለሁ። አንዴ ምንድን ነው የምለው።… ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወዳገርህ ሂድና ገላግለን!

81. SFX: ንጉሴ 'S FOOTSTEPS LEAVING

82. ዳንኤል : የሆነ ሰዓት ላይ አንድ ቦታ አገኝሀለሁ አንተ ከንቱ…

83. ምህረት: (breathing heavily from running) ዳንኤል … ማውራት … አለብን… አስቸኳይ ነው።

84. SFX: SCHOOL BELL RINGS

85. ዳንኤል : (still angry) አዝናለሁ አሁን ጥሩ ስሜት ውስጥ አይደለሁም። በዛላይ ትምህርት ሊጀምር ነው በኋላ እንገናኛለን (abandons her)

86. **SFX: ዳንኤል LEAVING**

87. ምህረት : ግን … **(sighs)**

88. **MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: ወ/ሮ ሉሊት, TWINS, AND አቶ ካሳሁን MEET AT ምህረት 'S SCHOOL</u>**

89. **SFX: SCHOOL ATMO OUTSIDE, STUDENTS PLAYING FOOTBALL**

90. **SFX: SEVERAL PEOPLE WALKING**

91. ቅዱስ : እማዬ የምህረት ት/ቤት ይሄ ነው? ተመልከች ያንን ትልቅ የእግር ኳስ ሜዳ።

92. ወ/ሮ ሉሊት: አዎ! ቅዱስ አይቸዋለሁ። ና አሁን – ምህረትን ፈልገን አባትህ ምን እንደሆነ እንንገራት።

93. ብሩክ : እንዴት ምህረት እንደዚህ የሚያምር ት/ቤት ልትገባ ቻለች? ለምንድን ነው እኛ የማንማረው?

94. ወ/ሮ ሉሊት: **(sighing)** ብሩክ፤ እህትህ እድለኛ ናት ነፃ የትምህርት እድል አግኝታ ነው። የኔ ሀሳብ አልነበረም። አሁን በጥያቄ ማጣደፍን አቁም። አሁን ስለተመለሳችሁ እናንተን ት/ቤት ለማስገባት እንሞክራለን። በመጀመሪያ ግን አባታችሁን ከእስር ቤት ማስለቀቅ አለብን። እስቲ አክስታችሁ ለምለም ጋ ለቦሪያ እንዴት ነበር ለምንድን ነው ከሷ ሸሽታችሁ የጠፋችሁት?

95. ቅዱስ : **(sad)** እሺ እማ ሁሉንም ነገር እንነግርሻለን።

96. **SFX: CAR DRIVING IN AT HIGH SPEED AND COMES TO A HALT**

97. ወ/ሮ ሉሊት: **(not amused)** ወይ ጉድ! ማን ነው እንዲህ ትምህርት ቤት ቅፅር ውስጥመኪና እያክለፈለፈ የሚነዳው?

98. **SFX: CAR DOOR OPENS AND CLOSES, FOLLOWED BY BEEPS**

99. ቅዱስ: **(afraid)** ወይኔ! እማዬ እሱ ነው እሱ ነው። መደበቅ አለብን።

100. ብሩክ: (fearful too) ጉዳችን ጉዳችን! መልሶ እንዳይወስደን ብቻ።

101. ወ/ሮ ሉሊት: (confused and shocked by the boys' reaction) ልጆች ምንሆናችኋል። ለምንድን ነው ታክሲ ውስጥ ያለውን ሰው ይህን ያህል ፈርታችሁ የምትንቀጠቀጡት።

**102. SFX: FOOTSTEPS FAST APPROACHING**

103. አቶ ካሳሁን: (sees ቅዱስ and ብሩክ ) ምን? እናንተ እዚህ ምን ታደርጋላችሁ? (clears throat and tries to act calm) እ - ይቅርታ እመቤት። እነሱን የሚመስሉ ልጆች አውቃለሁ። ግን ... ተሳስቼ ነው። የትምህርት ቤት ኋላፊዋን ለማግኘት ነው የመጣሁት። (in a hurry) መልካም ቀን።

104. ብሩክ: (trembling in fear) እማዬ! እንዲሄድ ንገሪው። አባክሽ ሊወስደን እንደማይችል ንገሪው።

105. ወ/ሮ ሉሊት: ይቅርታ ያድርጉልኝ እና ልጆቼ እርስዎን የፈሩ ይመስላል። ምክንያቱን ሊነግሩኝ ይችላሉ? እንደዚህ ያለ ፍርሃት በሰው ላይ አድሮባቸው አያውቅም።

106. አቶ ካሳሁን : እኔ ምን አውቃለሁ? የምንኖረው በትልቅ ዓለም ውስጥ ብዙ ሰዎች ብዙ ፊቶች ባሉበት ነው። -አሃ አሁን ገና ትዝ አለኝ ከተማ ውስጥ የምፈፅመው ጉዳይ አለኝ። መምህሯን በኋላ አገኛቸዋለሁ። ደህና ሁኑ ልጆች። አትፍሩኝ። (a little threatening) እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኛችሁት እንግዳ ነኝ።– አይደለም እንዴ?

**107. MUSIC INTERLUDE**

**108. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>**

በእዚሁ የዛሬውን መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ የተሰኘውን ድራማ ክፍል እንቋጫለን። ብሩክ እና ቅዱስ ለምንድን ነው አቶ ካሳሁንን ሲያዩ እንዲህ የተሸበሩት? ምህረትስ ከዳንኤል ማርገዟን ካወቀች በኋላ ምን ታደርግ ይሆን? ይህንን እና ሌሎችም «መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ» በተሰኘው በቀጣዩ እና የመጨረሻው ክፍል የመጀመሪያ ዙር ድራማ ላይ ትደርሱበታላችሁ። ይህንን ጭውውት ደግመው መስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን ይጎብኙ፤ አልያም በፌስቡክ አድራሻችን ላይ ይከታተሉ። እስከሚቀጥለዉ ጊዜ ጤና ይስጥልን።!